# በ16ኛው ክፍለ ዘመን በዐፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ካቶሊኮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን «ኦሪታዊ ናት» ሲሉ ስም ለማጥፋት ካካሄዱት ዘመቻ የተነሣ፤ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንቱ መልስ በመስጠት ያሳለፉትን ውሳኔ

በአብ ፥ በወልድ ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም በአንድ አምላክ ሃይማኖቴና የአባቶቼ እሥራኤላውያን ነገሥታት ሃይማኖት በመንግሥቴም (በረት) ግዛት ውስጥ የሚገኙ ምእመናን የመንጋዬ) ሃይማኖት ይህ ነው። እኛ በአንድ አምላክ ፥ በአንድ ልጁም በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ፤ ይኸውም ቃሉ ፥ ኃይሉ ፥ ምክሩ ፥ ጥበቡ ነው። ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር የነበረ ነው። በኋለኛው ዘመን ከመለኮታዊ መንበሩ ሳይለይ ወደ እኛ መጣ ፤ ከመንፈስ ቅዱስና ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆነ። በ፴ ዓመቱ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ፥ ፍጹም (ምሉእ) ሰው ሆነ። በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን በእንጨት ላይ ተሰቀለ ፣ ታመመ ፣ ሞተ ተቀበረ ፣ በሦስተኛውም ዕለት ተነሣ ፤ ከዚህ በኋላ በአርባ ቀን በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ ፥ በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ ፥ ዳግመኛም በክብር ይመጣል ፥ በሕያዋንና በሙታን ላይ ይፈርድ ዘንድ ፥ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ፥ ከአብ በሠረጸ ጌታ አዳኝ በሆነ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን። በአንዲት ጥምቀትም እናምናለን። ኃጢአትን ለማስተስረይ ፣ ትንሣኤ ሙታንን (የሙታንንም መነሣት) ተስፋ እናደርጋለን ፥ ለዘለዓለም ሕይወት ፥ አሜን።

እኛስ እውነተኛ በሆነው በጥርጊያውና በዋናው መንገድ እንሔዳለን ፤ ከአባቶቻችን ትምህርት ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ አናዘነብልም ፤

ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ፥

የጥበብ ምንጭ ጳውሎስ ፥

ሰባ ሁለቱ አርድእት ፥

በኒቂያ የተሰበሰቡ ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ኦርቶዶክሳውያን በቊስጥንጥንያ የተሰበሰቡ አንድ መቶ ሃምሳው ፥ በኤፌሶን የተሰበሰቡ ሁለት መቶው ፥ የናዖድ ልጅ የወናግ ሰገድ ልጅ በመንግሥቴ አጽናፍ ሰገድ የምባል የኢትዮጵያ ንጉሥ እኔ ገላውዴዎስ ፥ እንዲህ እሰብካለሁ እንዲህ አስተምራለሁ። ቀዳሚት ሰንበትን የምናከብርበት ምክንያት ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁንብን ብለው ክርስቶስን እንደ ሰቀሉት እንደ አይሁድ የምናከብራት አይደለምን። እነዚህ አይሁድ ውሃ አይቀዱም ፥ እሳት አያነዱም ፥ ወጥ አይሠሩም ፥ እንጀራ አይጋግሩም ፥ ከቤት ወደ ቤት አይሄዱም እኛ ግን የምናከብራት ሐዋርያት በዲድስቅልያ እንዳዘዙ ቅዳሴን በመቀደስና

ግብር (ማዕድ) በመሥራት ነው። (ሰንበቴ-ማኅበር-ተዝካር)እንደ እሑድ ሰንበት አይደለም የምናከብራት ይህችውም አዲሲቱ ዕለት ናት እግዚአብሔር የሠራት ዕለት ይህች ናት ፤ እንደሰትባት ሐሜትም እናድርግባት ብሎ ዳዊት ስለ እርሷ የተናገረላት። በዚህች ዕለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተነሥቶባታልና ፥ በዚችው ዕለት መንፈስ ቅዱስ በጽርሐ ጽዮን ማኅፀን ሰው ሆኗልና ፤ በዚች ዕለት ዳግመኛ ይመጣል ፥ ለጻድቃን ሽልማት ለኃጥአን ውርደት (ዕዳ)።

ስለ ሥርዓተ ግዝረትም እንደ አይሁድ የምንገዝር አይደለንም የጥበብ ምንጭ የጳውሎስን ትምህርት እናውቃለንና።-«መገዘር አይጠቅምም ፥ አለመገዘርም ግዳጅ አይደለም። አዲስ ፍጥረት ነው እንጂ ይኸውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው። ዳግመኛም ለቆሮንቶስ ሰዎች «የተገዘረ ቁልፈትን አይሻ» አለ። የጳውሎስ የትምህርቱ መጽሐፍ ሁሉ በእኛ ዘንድ አለ። ስለ ግዝረትና ስለ ቁልፈት ያስተምረናል። ነገር ግን በእኛ ዘንድ ያለው ግዝረት እንደ ኢትዮጵያና እንደ ኖባ የፊት መተልተል እንደ ሕንድ ሰዎች የጆሮ መነደል ያለ የአገር ልማድ ነው። ይህን የምናደርገው በኦሪት ሕግ አይደለም። በሰው ልማድ ነው እንጂ።

አሣማንም ስለ መብላት ፥ ከመብላት የተከለከልነው እንደ አይሁድ የኦሪትን ሕግ ለመጠበቅ ብለን አይደለም። የሚበላውንም አንጸየፌውም አናረክሰውም ፤ የማይበላውንም ብላ ብለን አናስገድደውም ፥ አባታችን ጳውሎስ ለሮም እንደ ጻፈው «የሚበላ የማይበላን አይንቀፈው (አይናቀው)እግዚአብሔር ሁሉንም ተቀብሏቸዋልና የእግዚአብሔር መንግሥት በመብልና በመጠጥ አይደለችም። ለንጹሐን ሁሉ ንጹሕ ነው ፥ ለሰው ክፉው ከጥርጣሬ ጋር መብላት ነው። ወንጌላዊ ማቴዎስም -«ከአፉ ከሚወጣው በቀር ሰውን የሚያረክሰው የለም ፤ ወደ ሆድ የሚገባ ጥቂት ቆይቶ ይወድቃል ፥ ይፈሳል ፥ ምግቦችን ሁሉ ያነጻል»አለ። ይህ አባባሉ ከኦሪት መጽሐፍ የተማሩ የአይሁድን የስሕተት ሕንጻ ሁሉ አፈረሰው። የእኔና በግዛቴ ውስጥ ያሉ በትእዛዜ የሚያስተምሩ አዋቂዎች ካህናት ሃይማኖት ይህ ነው። ከወንጌል መንገድ ፥ ከጳውሎስም ትምህርት ወደ ቀኝና ወደ ግራ አይሉም። በእኛም የታሪክ መጽሐፋችን ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ በግዛት ዘመኑ የተጠመቁትን አይሁድ ሁሉ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ዕለት ያሣማ ሥጋ እንዲያበሏቸው አዘዘ የሚል ጽሑፍ አለ።

ነገር ግን ሰው በልቡ ደስ እንዳለው የእንስሳትን ሥጋ ከመብላት ይወሰናል፦ የአሣ ሥጋ የሚወድ አለ ፤ የዶሮ ሥጋ መብላት የሚወድ አለ። የበግ ሥጋ ከመብላት የሚወሰን አለ። ሁሉ ለልቡ ደስ ያለውን ይከተላል። የሰው ውዴታውና ፈቃዱ እንደዚህ ነው። ስለ እንስሳት ሥጋ መብል በአዲሲቱ መጽሐፍ ውስጥ (አዲስ ኪዳን) ሕግም ቀኖናም የለም። ለንጹሐን ሁሉ ንጹሕ ነው ጳውሎስም ፦«የሚያምን ሁሉን ይብላ» አለ የሃይማኖቴን እውነት ታውቅ ዘንድ ይህን ሁሉ ለመጻፍ ተጋሁ። ዳሞት በሚባል አገር በሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ተጻፈ።

- - - - - - - - - - - - - -

ከክርስትና በፊት ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን ለመቀበሏ የታሪክና የጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ዘንድ ሲሠራባቸው የሚኖሩ አያሌ ልማዶችና ባህሎች አሉ ፤ እነዚህ የብሉይ ኪዳን ልማዶችና ባህሎች በአሁኑ ጊዜ ፥ ማለት በክርስትና ሃይማኖታችን ውስጥ እንደ ዶግማ ወይም እንደ ቀኖና ሳይሆኑ እንደልማድ ሆነው የሚጠበቁ ናቸው። እነዚህም፦

ሀ/ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዳይበሉ የሚከለክሏቸውን እንስሳትና አዕዋፍ ዛሬም የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች አይመገቧቸውም። ይህ በወንጌል ለሚያምን ሁሉ የተከለከለ አይደለም ፥ ከላይ እንደገለጥነው እኛ ግን ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ልማድ መሠረት ነው።

ለ/ ግዝረት ፥ በብሉይ ኪዳን ለማመን ምልክት ሲሆን በአዲስ ኪዳን ግን በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ መለያ ምልክታቸው ወይም ማኅተማቸው ጥምቀት ነው። በሀገራችን ግን ከብሉይ ኪዳን በተወረሰው ልማድ ልጅ ሲወለድ ይገረዛል ፥ ግዝረቱ ግን የሕግ ሳይሆን የፈቃድ ነው ፥ ይህም ማለት በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ግዝረት ሕግ አይደለም ፤ ምእመናን ልጆቻቸውን ቢያስገርዙም ባያስገርዙም የራሳቸው ፈቃድ ነው ፤ ማለት ነው።

ለምሳሌ ያህል እነዚህን ሁለቱን ጠቀስን እንጂ ጠቅላላው በሕዝቡ የኑሮ ሥርዓትና ሃይማኖታዊ ስሜት ፥ በኀዘንና በደስታ ጊዜ ያለው ሁኔታ የበዓላት አከባበር ፥ የሴቶችና የሕጻናት ጌጣጌጥ ሁሉ ፦ የብሉይ ኪዳንን ሥርዓትና የሴማውያንን ሥልጣኔ የሚያሳይ ነው። በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ የማኅሌት ሥርዓት ፥ የካህናቱ ልብሰ-ተክህኖ ፥ ካባው ፥ ድርቡ ፥ ጸናጽሉ ፥ ከበሮው ፥ ኩፋሩ ፥ መጠምጠሚያው ፥ የታቦቱ ክብርና ሌላውም ሁሉ ከብሉይ ኪዳን ሥርዓት ጋር ይመሳሰላል። ይህ ሁሉ የሚያሳየው ከክርስትና በፊት ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ሀገር እንደነበረች ነው። በሌሎች ከአረማዊነት በተመለሱ ሀገሮች በግሪክ ፥ በላቲንና በሌሎችም ይህ ሁሉ አይታወቅም። አንዳንድ የአረማዊነት ጠባይ ግን ይታይባቸዋል። የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መምህራን ሐዋርያትና ሊቃውንትም በጥንተ ስብከታቸው ሃይማኖትን የሚጐዱ ልማዶችን ብቻ እንጂ የሕዝቡን ጥቃቅን ልማድ ግን ማጥፋት አስፈላጊ መስሎ ስላላገኙት ብዙ አልታገሉለትም። ስለዚህም ፦ ከብሉይ ኪዳን የተመለሱት እንደ ኢትዮጵያ ያሉት አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች ሲኖሯቸው ፥ ከአረማዊነት የተመለሱት ደግሞ በአረማዊነት በነበሩበት ጊዜ የሚበሏቸውን ይበላሉ ፥ ግዝረትም ምን እንደሆነ አያውቁም።

በሃያኛው መቶ ዘመን በጥንት ቅርሶች ጥናት (Archeology) በኢትዮጵያ ውስጥ በየሀና በአድቤደራ በሌሎችም ሥፍራዎች አያሌ የጣኦት ምስሎችና የቤተ ጣኦት መገልገያ ዕቃዎች እየተቆፈሩ ወጥተዋል ፥ የጣኦት ቤተ መቅደሶችና የፀሐይና የጨረቃ ምስል የተቀረጸባቸው የመገበያያ መሐለቆች ተገኝተዋል። አንዳንድ ባለታሪኮችም እንደሚሉት፦ በአክሱም ነግሦ የነበረው አይዛና (ኤዛና) (ምናልባት የአብርሃምና

የአጽብሐ አባት ሳይሆን አይቀርም) ራሱ የረቂቁ የማሕሬም ልጅ ነኝ እያለ ይጠራ ነበር ብለዋል። «ማሕሬምን» ግሪኮች «አሪስ» ይሉታል። የጦር ፥ የጦረኞች ፥ የጀግኖች ፥ የአርበኞች አምላክ ማለት ነው። ይኸው ማሕሬም ለብዙ ዘመን ለአክሱም ንጉሣውያን ቤተሰብ ዑቃቢ አምላክ ሳይሆን አልቀረም። በኋላ ግን ይኸው አይዛና ኑብያን ድል አድርጎ ከያዘ በኋላ ምንም ዓይነት የጣኦት ስም አላነሣም ፤ ያገኘውም ድል የሰማይ አምላክ ድል እንጂ የእርሱ እንዳልነበረ ጽፏል። «በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው በሰማይም በምድርም ለዘለዓለም የሚገዛ» ብሎ ድል የሰጠውን አምላክ ገልጧል። ፲፮/ በአይዛና በመጀመሪያው የግዛት ዘመኑ የተሠሩ መሐለቆች የጣኦታት ምስል ፥ የግማሽ ጨረቃና የከዋክብት ምስል ነበረባቸው ፤ በኋላ የወጡት መሐለቆች ግን መስቀል ቅርጽ ታትሞባቸው ነበር። እዚህ ላይ በአጭሩ የተገለጠው በጥንታዊ ቅርስ መርማሪዎችና በባለ ታሪኮች የተከሠተው የአረማውያን ኅብረ አምሳል የፊተኛውን ታሪክ አይንደውም ፤ በጣኦት ማምለክና የአሕዛብን ልማድ በማደኀ መውሰድ ከከነዓን ውጭ ይቅርና በከነዓንም ምድር የተለመደ ነበር ፤ ለልዑል እግዚአብሔር መመስገኛ ቤተ መቅደስን ለመጀመሪያ ጊዜ የሠራው ሰሎሞንም እንኳ ለግብጻዊት ሚስቱ መስገጃ ቤተ ጣኦት አሠርቶ ነበር። ይህን የመሰለ አድራጐት በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ተነግሯል። ነገር ግን የእሥራኤል እምነት የሚነገረው በአንድ አምላክ ማመናቸው ነው ፤ መታወቂያቸውም ይኸው ነው። በኢትዮጵያም እንዲሁ ነው ፤ ብዙ የተለያዩ መሪዎች እየተነሡ ለአመራር እንዲመቻቸው ሲሉ ብዙ ነገሮችን ቢለውጡና ቢያዳቅሉም ፥ የሀገሪቱንና የሕዝቡን ታሪክ አይለውጠውም። ስለ ኢትዮጵያ የሃይማኖትና የሞራል ክብር የተናገረ ሶፎንያስ፦ ኢትዮጵያ በአንድ አምላክ የምታምን ሀገር መሆኗን ሲገልጥ፦ «እምነ ማዕዶተ አፍላገ ኢትዮጵያ ያመጽኡ ሊተ መሥዋዕተ» ፦ «ከኢትዮጵያ ወንዝ ወዲያ ማዶ የሚሰግዱልኝ የተበተኑት ልጆቼ መባዬን ይዘው ወደ እኔ ይመጣሉ»ብሏል። ይህም አነጋገር ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ኢየሩሳሌም ድረስ ሄዶ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምኖ በተጠመቀ ጊዜ ተፈጽሟል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ከአቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘሸዋ